# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

## የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ

## የታክስ ከፋዩን ሀብት ስለመያዝ እና ስለመሸጥ የወጣ

## መመሪያ ቁጥር 5/2012

ህዳር / 2012 ዓ/ም

ባህር ዳር

# የታክስ ከፋዩን ሀብት ስለመያዝ እና ስለመሸጥ የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2012

**1. አውጪው ባለስልጣን**

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 አንቀጽ 135 ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

**2. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የታክስ ከፋዮችን ሀብት ስለመያዝ እና ስለመሸጥ የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2012**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡

**3. ትርጓሜ**

በታክስ አስተዳደር አዋጁ ትርጉም የተሰጠው ቃል ወይም ሀረግ በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለ እንደሆን በታክስ አስተዳደር አዋጁ የተሰጠውን ትርጉም ይይዛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም፡-

1) **"ሀብት "** ማለት የመያዣ ትዕዛዝ ሊወጣባቸው ከማይችሉት ሀብቶች በስተቀር ታክስ ከፋዩ በሊዝ የያዘውን መሬት ጨምሮ ማናቸውም ቤት ወይም ህንጻ፣የንግድ ሥራ የሚከናወንበት ድርጅት፣ልዩ ልዩ እቃዎች፣በሌላ ሰው ዘንድ ያለው ወይም በሌላ ሰው የሚገኘው ወይም የሚከፈለው ገንዘብ፣ቼኮች፣ የሚተላለፉ ሰነዶች፣ቦንዶች ወይም ለገንዘብ የተሰጡ ሌሎች ዋስትናዎች፣በኩባንያ ውስጥ ያለው የአክሲዮን ድርሻዎች፣በጋራ በተያዙ ሀብቶች ያለው ድርሻ ወይም ማናቸውም ሊሸጡ የሚችሉ ሌሎች ሀብቶች ናቸው፡፡

2) **"ሀብት ማስከበር"** ማለት የገቢዎች ቢሮ የታክስ ከፋዩን ሀብት ወይም ንብረት ከመያዙ በፊት ባለበት እንዲቆይ እና እንዳይንቀሳቀስ የሚወስደው እርምጃ ነው፡፡

3) **"መያዣ"** ማለት በማናቸውም መንገድ የታክስ ከፋዩን ሀብት መያዝ እንዲሁም የታክስ ከፋዩ የሆነ ገንዘብ/ሀብት በእጁ ከሚገኝ ሰው ታክስ መሰብሰብን ይጨምራል፡፡

4) **"ታክስ"** ማለት በገቢ እቃዎች ላይ የተጣለን ቀረጥ፣ ታክስ እና አስተዳደራዊ ቅጣትን ይጨምራል፡፡

5) **"የገቢዎች ቢሮ "** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ መምሪያዎችን፣ጽ/ቤቶች እና የቀበሌ ማእከላትን ይጨምራል፡፡

6) **"ኃላፊ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ገቢዎች ቢሮ ኃላፊ ሲሆን በየደረጃው የሚገኙ መምሪያዎችን፣ጽ/ቤቶች እና የቀበሌ ማእከላት ኃላፊን ይጨምራል፡፡

7) **"አዋጅ"** ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 241/2008 ነው፡፡